# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ቅጽ 38 ቁ. 5 ሰኔ 2005 ዓ.ም


## ነጻነት ለተጠማ፤ ምክር ለሚሰማ

ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ሰባ ዓመት ይደናቆሩ እንደተባለው ዛሬ ድርጅቶችና በፖሊቲካው መድረክ አለን ቁጠሩን የሚሉ ቡድኖች በፈሉበት ወቅት ካለፈው ትግልና መስዋዕትነት ተመክሮን መቅሰሙ ከብዶ ስህተቶችን መደጋገሙ ሰፍኗል። የዚህ ስህተት ዓይነታ መለያው ደግሞ ገና ሀ ብለው መቦደን ወይም መደራጀት ሲጀምሩ በሀገራችን በዘመናዊ የፖለቲካ ድርጅትነት የመጀመሪያው ሆኖ ስንት ተመክሮ የቀሰመውንና ዛሬም ህልውናውን ጠብቆ ያለውን ኢሕአፓን ማጥቃትና መወንጀልን አምርረው ይያያዙታል። ድርጅት ሲሉ ድርጅት ስንል በሚል በተደጋጋሚ የተቸን ቢሆንም ዛሬ ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ኢሕአፓን ልዩ ያደረጉትን መሠረታዊ ይዘቶችና ተግባሮች፤ አቅዋሞችና መርሆዎች መጥቀስ እንፈልጋለን ። ኢሕአፓ ማንነቱ በስሙ ይገለጻል--ኢትዮጵያዊና ለኢትዮጵያ የቆመ ነው፤ ሕዝባዊና ለብዙሃኑ ጥቅም የሚታገል ነው፤ ለስር ነቀል ለውጥ ለአብዮት የተዋደቀ ነው። ግቡን ለማድረስ በድርጅት መልክ በፓርቲ መልክ ሙያተኛ ሆኖ በሕግና ደምብ፤ በስነ ሥርዓትም መሠረት የታገለና በመታገልም ላይ ያለ ነው -የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ። የኢሕአፓን ይዘት ለመረዳትም ድርጅቱ የተቋቋመብትን ተጨባጭ ሁኔታ--ማለትም የሀገራችንንም ሆነ ዓለም አቀፋን ሁኔታ መገንዘብ ያሻል። ያለፈው ጊዜ የሚረሳ የሚመስላቸው በስህተትና በታሪክ ብረዛ የአፄው ዘመን ጭቆና አልባ ነበር የሚሉና ብዙሃኑን ለበደሉት ንጉሥ ውዳሴ የሚደረድሩ ቢበዙም ሐቁ ግን የአፄው ሥርዓት ሰፊውን ሕዝብ የጨቆነና የበዘበዘና በፊውዳል ጨለማ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያቆየ ነበር። ኣርሶ አደሩ ጢሰኛ ገባር ነበር--በሕግ ሁለት ሶስተኛ ምርቱን ለባላባቶች የሚገብር። ሠርቶ አደሩም በድህነት ሲማቅቅ የቆየ ከመሆኑ በላይ የመደራጀት መብቱ የታፈነበት፤ አሊያም ለባዕዳን ተገዢ እንዲሆን የተደረገበት (እነ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅና በሆላንድ ዘረኞች ስር የነበረውን ወንጂን ያስታውሷል) አስቃቂ ሁኔታ ነበር። ወቅቱ ስዩመ መለኮት የተባሉት አፄም ሥልጣናቸው የማይደፈር የማይገረሰሥ ተብሎ የታወጀበት፤ የይስሙላ ፓርላማ ቢኖርም የሕግ የበላይነት የጠፋበት፤ ደሞክራሲያዊ መብቶች ሁሉ ታፍነው ፤ ረሐብም ሰፍኖ ቡትቶ ለባሽ ሕዝብ ተደርገን የነበርንበት ጊዜ እንደነበር የምንረሳው አልነበረም ። ያኔም እንደ ዛሬ ኢትዮጵያ ለጥቂቶች ገነት ስትሆናላቸው ለብዙኃኑ ግን እንደተባለው እሰር ቤት ነበረች። ሊካድ የማይችለው ሐቅ ይህ ነበርና ሰፊው ሕዝብ በላቡ ያስተማራቸው ተማሪዎች በአፄው ሥርዓት ላይ አመጹ። ቀደም ሲልም የተማሩ ምሁራን፤ ለሕዝብ ብለው የተነሱ መኮንኖች፣ ላብደሮችም ለለውጥ ታግለው ነበር። በላይ ዘለቀን፤

መንግሥቱና ገርማሜ ንዋይን፤ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያትን፤ ጥላሁን ግዛውንና ለሎችንም ሁሉ ማን ሰቀለ? ማን ገደለ? መልሱ ጨቋኙና አምባገነኑ የአጼው ሥርዓት የሚል ነው።

ኢሕአፓ የዚህ ሁሉ የሕዝብ ትግል-- የአርሶ አደር የተሰበጣጠሩ አመጾች፣ የተማሪዎች ትግል፣ የላብ አደሩ ንቅናቄ፣ ...ወዘተ--ማለትም ከሕዝብ መከራና ሰቆቃ፤ ከሕዝብ የለውጥ ፍላጎትና የብሩህ ቀን ተስፋ፤ ከሕዝብ የነጻነትና የመብት ጥም የተወለደ ነበር። ሐቁን ማወቅ ሆነ መቀበል የተሳናቸው ግን የማያውቁትን በመጽሐፍ ሳይቀር ጠርዘው ውሸትን ሊቸረችሩ የተነሱት ሁሉ የኢትዮጵያ ልጆችን ሐቅኛ ትግል በሌላ መልክ እያቀረቡ አዲሱን ትውልድ ያደናግራሉ። ኢሕአፓ የተመሠረተው በባዕዳን ሳይሆን ለሕዝባቸው ሊታገሉ ቆርጠው በተነሱ የኢትዮጵያ የራሷ ልጆች ነው። ራሳቸውን ኢትዮጵያዊ፤ ትግላቸውንም ለኢትዮጵያ ብለው የተነሱ። በመጀመሪያም መሬት ለአራሹ ብለው የፊውዳሉን ስርዓት ማገር፣ ምሰሶ ሲነቀንቁ በችኩልነትና አላዋቂዎች እንደሚሉት በባዕድ ርዕዮትና ቅኝት ሳይሆን ለአያሌ ዓመታት ለአፄው አቤቱታን ሲያሰሙና ለውጥን ሲጠይቁ ቆይተው ነው። ለነገሩ ኢሕአፓ ደርግ አብዮትን ማጅራት ሲመታ ሆነ ወያኔ ራሱ ሥልጣን ያዝኩ ሲል የሕዝብ የዴሞክራሲ መብት ከተከበረ በሰላም ሊታገል ዝግጁ መሆኑን በይፋ ገልጾም ነበር። ያገኘውን አሉታዊ ሞላሽና የደረሰበትን ጥቃት ታሪክ የሚረሳው አይደለም ። ኢሕአፓ በተመሰረተበትና ትግሉም በተደራጀ መልክ ሊካሄድ በተነሳበት ወቅት ዓለማችን ትናጥ የነበረው በሕዝቦች የነጻነትና የመብት ተራማጅ እንቅስቃሴ ነበርና ኢሕአፓም ከዚሁ ዝንባሌና ርዕዮት የሚርቅበት ምክንያትም ሁኔታም አልነበረም። በመሆኑም ድርጅቱ ለላብ አደሩና አርሶ አደሩ፤ ለሰፊው ሕዝብ መብት፤ ሕዝባዊ ለሆነ ዴሞክራሲ፤ ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ... ወዘተ በመታገሉ የሚያሰማው ጸጸትና የሚቆጨውም ቅንጣት ታህል ነገር የለም። ወጣቱና ኢሕአፓ በባዕድ ርዕዮት ተገፍተው፣ ...ወዘተ እንቅስቃሴ አደረጉ ብለው ለሚጮሁት ሁሉ ያለው መልስ ካፒታሊዝምም ሆነ የምዕራቡ ርዕዮት ሀገር በቀል አይደለም የሚል ይሆናል። መሬት ለአራሹ፤ መብትና ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ፤ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ይከበር፤ ...ወዘተ ብሎ ለሕዝብና ለሀገር መታገል ያስመሰግናል እንጂ ከቶም አያስወቅስም። መስዋዕትነትን በፀጋ የተቀበለው ኢሕአፓ ያነሳቸውና የታገለላቸው የሕዝብ መሠረታዊና ወሳኝ ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽን ጠያቂ ሆነው መገኘታቸው ድርጅቱ ምንኛ ከሕዝብ ፍላጎትና ተስፋ ጋር እንደሰመረ ያረጋግጣል። በሆነው ምክንያት የሕዝብን ፍላጎትና ጥቅም ተጻሮም አያውቅም። ሐቁ ይህ ነው። በዚህም ከሌሎች ይለያል፤ እስከዛሬ።

ኢሕአፓ በአቅዋሙ ልዩ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ነጥቦች አንዳንዶቹ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት የሚመለከቱ ናቸው--ማለትም ከባድና ወሳኝ ጉዳዮች። ኢሕአፓ ራሱን የኢትዮጵያ ብሎ ተደራጀ ተነሳ እንጂ ወደ ጎጥና ብሔረሰብ ወርዶ ግንጠላን አላቀነቀነም። በጥያቄው ዙሪያ ለነበረው ጭቆና--አዎ ያኔም እኩልነት ሰፍኖ አልነበረምና-- አንድነትን ያጠናክራል፤ ይደግፋል በሚል ያቀረበው አቅዋም ዛሬ ተቺዎች ቢበዙበትም ድርጅቱ በሕዝብ መሀል በብሔረሰብ፣ በጾታና ሃይማኖት የተነሳ ልዩነት ተወግዶ በዴሞክራሲ መሠረት አንድ ኢትዮጵያ እውን ትሁን ብሎ ታግሏል። አቅዋሙም ብዙዎችን በኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ግቡ ሊያሰባስብና ሊያታግል አስችሎታል። ኢሕአፓ ደርግ መንግሥታችን ነው ብሎ ከፋሺስቶቹ ጋር አላበረም። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ እንደ ወያኔ አቅዋም አልወሰደም። ትምክህትንም ጠባብነትንም አጥብቆ በመታገሉ ሁሉም በየፊናቸው ዘምተውበታል፤ አጥቅተውታል። የወያኔ ቡድን ብሔረሰቦች የሸዋን የበላይነትና የአማራ ጭቆናን ታግለው የየራሳቸውን መንግሥት መመሥረት አለባቸው ብሎ መርሀ ግብሩን ሲያወጣና የርስ በርሱ ቅራኔ ዋና ነውና አብሮ መኖር ከቶም አይታሰብ ሲል፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ፣ አንድነትና ሁኔታንም መሠረት አድርጎ የታገለው ዋናው ኃይል ኢሕአፓ መሆኑን በደም የተጻፈ ታሪክ ይመሰክራል። ኢሕአፓ ዛሬም ለኢትዮጵያ አንድነት ዘብ የቆመና መስዋዕትነትንም እየከፈለ ያለ ድርጅት ነው እንጂ ለሥልጣን ለበቃ ዘረኛ ተጎንብሶ ፍርፋሪ እየተቀበለ ውድ ሀገራችንን ቅርጫ አላስገባም፤ አልቦጠበጠም።

ከኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አንጻርም ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ እንዳትደፈር ታግሏል። ነጻና

ሉዓላዊነቷ የተከበረ ኢትዮጵያ የሚለው መርህ ግብሩ በኢትዮጵያ መሬት ማንም የባዕድ ኃይል የጦር ሠፈር አያቋቁምም፤ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ይከበራል፤ ኢትዮጵያ የማንም ባዕድ ኃይል ሎሌ አትሆንም፤ ገለልተኛና ለነጻነት የሚታገሉትንም የምትረዳ ትሆናለች የሚል ነበር፡ ነውም። በመሆኑም የአፄውን አገዛዝ እየረዳ፤ በሀገራችን የጦር ሠፈር ያቋቋመውንና የለውጥ ጥረቶችን/ ሁሉ ከሥርዓቱ ጋር ተባብሮ ያከሸፈውን (ለምሳሌ የ1953-ቱን የነመንግሥቱና ገርማሜ ንዋይ የመፍንቅለ መንግሥት ሙከራ) ባዕዳን ኃይላት ከሀገር ይውጡ፤ ጣልቃ ገብነታቸውም ያብቃ ብሎ ተቃውሞውን አሰምቷል። በአፍሪካ ደረጃ የነጻነት ትግሉን ሁሉ ያጠቁትን፤ አፓርታይድን የደገፉትን፤ እነንክሩማህን የገለበጡትንና ሉሙምባንም አስገድለው በከሃዲው ሞቡቱ የተኩትን ምዕራብ ኃይሎች ኢሕአፓ ተቃውሟል፤ ታግሏል። ያኔም ዛሬም የነዚህ ኃይሎች ቡችላ የሆኑትንም እያጋለጠ ተቋቁሟቸዋል። ዛሬም ወያኔን ለሥልጣን ያበቁትን እነአሜሪካንና፤ አሁንም ከዘረኛው አገዛዝ ጎን ቆመው ያሉትን ምዕራባውያንና ሌሎችንም ኢሕአፓ ድርጊታቸውን ይቃወማል። ለአምባገነኑ ኃይል የሚሰጡትን እርዳታና ትብብር እንዲያቆሙ ድምጹን ያሰማል። የኢትዮጵያ ክብርና ሉዓላዊነት ይህን ያላሰለሰ ትግል ይጠይቃልና።

የአረመኔው ደርግ አባላትና ርዝራዦች እንዲሁም --ጉድ እንበልና - ወያኔም ኢሕአፓ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ከባዕዳን ጋር ተባብሮና ተሰልፎ ነበር ብለው ሲቀበጣጥሩ መስማት ተደጋጋሚ ሆኗል። ወያኔ ለግብጽ፣ ለሱማሌ፣ ለገዳፊ፣ ለአረቦች ሁሉ አድሮ ያን ሁሉ ወንጀል ያልፈጸመ ይመስል ዓይኑን በጨው አጥቦ ኢሕአፓን ይከሳል። ማን ተከዜን ድልድይ ሊያፈርስ ተነሳ? ማን ለስደት የሚሸሹትን ደቡብ ሱዳኖች እየያዘ ለሱዳን አስርክቦ በየእርሻው ቦታ (መሸሩፅ) አስረሸነና በክፍያ መሣሪያ ተረከበ? ማን ሲሶ ኢትዮጵያን ምዕራብ ሶማሊያ ነው ብሎ ለዚያድ ባሬ ፈርሞ ቢሮና መሣሪያ ተሰጠው? ማን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት መገንጠል አለባት ብሎ ከነሻዕቢያ ሙሉ ድጋፍ አገኘ? አረመኔው ኮለኔል የሶማሊያን ወረራና ጥቃት ምክንያት አድርጎ ሕዝብን በብሔራዊ ስሜት ቀስቅሶ በዚያውም ኢሕአፓን ለመምታት ሲል በሐሰት ድርጅቱ ዚያድ ባሬን ደገፈ ብሎ ያሰራጨውን በተመለከተም ኢሕአፓ ይህን አለማድረጉን ደግሞ ደጋግሞ አስረድቷል። ሁለት አድሀሪ አገዛዞች የሚጭሩት ጦርነት የሕዝብን ጥቅም ተጻራሪና ትኩረትን አንሻዋራሪ መሆኑን በውቅቱም የገለጸው ሲሆን ወያኔም ከሻዕቢያ ጋር ባድሜ ብሎ እንፋለም ሲለን ይህም ሌላ ወጥመድ ነው ብሎ ሊያስጠነቅቅ ሞክሮ ነበር። ወያኔ ሕዝብን አስፈጅቶ የሀገርን መሬት በፈረንጅ ውሳኔ ሊያስረክብና ይህንንም ድል ሊል ሲነሳ ኢሕአፓ ማጋላጡም የሚረሳ አይደለም። ዛሬም ትልቅ ግድብ በሚል እያደናገረ ሕዝብን ከግብጽ ጋር ጦርነት ውስጥ ለመክተት ሲቅበጠበጥ አጋልጠነዋል፤ ተንኮሉንም ውድቅ ለማድረግ ድርጅቱ እየጣረ ነው ሱዳን የአባይ ድልድይን አፍርሱልኝ ስትል ኢሕአፓ የሀገርን ጥቅም ለመሣሪያ ሸጦ እሺ አላለም። ሱዳን ዛሬ በወያኔ ፍቃድ የወሰደችውን ነፍሶ ገብያ ቋራ ልትወር ስትከጅል ኢሕአፓ ህዝብን ከተት ብሎ የሰፈሩትን ሱዳኖች አባረረ እንጂ ለሱዳን ድለላም ሆነ ማስፈራሪያ አልተንበረከከም። ቻይና፣ ሩስያና ደቡብ የመን ደርግን ደግፉ ሲሉ ድርጅቱ እምቢኝ አለ እንጂ ካላችሁ ብሎ እጅ አልሰጠም። ከጠባቦች ጋር ሆነው በኢትዮጵያ ላይ ያሴሩትንም ሁሉ ተቃውሟል እንጂ ዝም አላለም። ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ በላይና ተቀዳም ቀዳሚ ያደረገው ማንም ሀገር፣ ጉዳይ ወይም ፍላጎት አልነበረም፤ ዛሬም የለም፡፡ ይህ የፀና ኢትዮጵያዊነት፤ ወደ ታች ዝቅ የማይልና የማይጠብ ሀገራዊ ብሔራዊ ስሜት ድርጅቱን ልዩ አድርጎት ቆይቷል። አሌ ሊሉ የከጅሉትንም ሁሉ ውሸትና ስንቅ እያደር ይቀላልን አስተርቶባቸዋል።

የኢሕአፓ ኢትዮጵያዊነት በጽኑ ይዘቱ ሀገርን ማዕከል ባደረገው ትግሉ እንደሚገለጸው ሁሉ ዴሞክራሲ ስንል፤ እኩልነት ስንልና ሌሎችም ይህን ሲሉ በሚለው ላይ ያለው ልዩነት በጣም ሰፊ ነው። ምርጥ መኮንኖች የሕዝብን አብዮት አፍነው ለሥልጣን ሲበቁና ራሳችውን ጊዜያዊ መንግሥት ብለው በሞግዚትነት ሲሰይሙ ኢሕአፓ ገና ከጠዋቱ አምሮ ተቃውሟቸዋል፤ ፖለቲካዊ ትግልንም አፋፍሞባቸዋል። ዴሞክራሲ በገደብ ብለው ሕዝብን እንደ አላዋቂ ፈርጀው ሊያታልሉና በኢትዮጵያ ትቅደም ሊሸነግሉም ሲነሱ ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት (ወያኔንም ወታደሩንም ያቀፈ)

ብሎ ዴሞክራሲ ላይ ገደብ መጣል እንደማይቻልና እንደማይገባ አጽንኦት ሰጥቶ በመዋደቅ የደርግን አምባገነናው ይዘት አጋልጦ በታሪካችን ከታዩት የሕዝብ የፖለቲካ ትግሎች መካከል ድንቅ ሆኖ በታሪክ የተመዘገበውን ትግል አካሂዷል፤ ሕዝብም ይህን ትግል ደግፎ ከድርጅቱ ጎንና ዙሪያ ቆሞ መስዋዕትነትን ተቀብሏል። ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትና ደሞክራሲያዊ ሽግግር የነበረውን እድል ደርጎች አበላሹት። ዴምክራሲ ስንል በቅድሚያ ሰፊውንና ጭቁኑን ሥርቶ አደር ሕዝብ የሚመለከትና ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ይዘቶች ያሉት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ለጥቂቶች ዴሞክራሲ ለብዙኀኑ ደግሞ መረገጥ (በወያኔ) ከይሲ ሊሆን አይችልም። ላለፉት 20 ዓመታት የሚያገኙትም ቢሆኑ ዘረኛ፣ ፀረ ኢትዮጵያና አምባገነናዊ የሆነውን አገዛዝ ደሞክራሲያዊ ነው ብለው ያሞካሹታል። "ታማኝ ውሻን ጃስ ይበሉ" ነውናም ባዕዳንም አገልጋያቸውንና ተላላኪያቸውንም ዴሞክራሲያዊ ብለው ሲያመሰግኑና ሲዋሹ ታዝበናል። ወያኔና ዴሞክራሲ ግን ሰማይን መሬት ያህል መራራቃቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል።

ወያኔ ለሥልጣን በባዕዳን ድጋፍ ከመብቃቱ በፊትም ሕዝብን እየከፋፈለና እያደናገረ መንቀሳቀሱ የሚታውቅ ነው። በቅድሚያ የትግራይን ሕዝብ በጠባብ ብሔርተኛነት ሊበክልና ፀረ-ሸዋ ፀረ-አማራ በሚል ጻያፍ ዝንባሌ ሊያጠምድ ሞከረ፤ አደናገረ። ለጥቆም ሌሎች ብሔረሰቦችንም በየቡድኑ አማካኝነት በዚሁ ፀረ-አማራ በሚል ቅኝት ሊበክል ሊያራርቅ ጣረ። ኢትዮጵያ ባሉ ድርጅቶች ላይ (ኢሕአፓና ኢዲኅ ለምሳሌ)የሀሰት ልፈፋውንና የጭቃ ጅራፉን ካጮኸ በኋላም ከደጋፊዎቹ ጋር ሆኖ ጦርነት አውጆባቸው ወግቷቸዋል። ወያኔ የያዘው መንገድ አላዋጣ ሲለውም የግንጠላ ጫጫታውን ሙያ በልብ ኣድርጎ ኢሕአዴግ የሚል ጭምብል አጥልቆ በርከት ያለውን ዜጋ-- በተለይም በውጭ ሀገር ያለውን-- አደናገረ። ይህን ኢሕአዴግ ተብዬ መጋዣ ምን ያህል እንደተጠቀመበትና እየተገለገለበትም እንዳለ እያየነው ያለ እኩይ ተግባር ነው። የለንደን ጉባዔ ሆነ የአዲስ አበባ የሽግግር ተብዬ ጉባዔ ላይም ሀገር ወዳድ ድርጅቶች እንዳይወከሉ አድርጎ--እርስ በርስ የሚቃረኑ ሰበብ አስባቦችን ደርድሮ-- ከመቅጽበት የተፈለፈሉን አቅመ ቢስ ቡድኖች ኮልኩሎ፤ ትምክህተኛ ባላቸውና ጠላት ባለው ሕዝብም ላይ አስጨሆ፤ የራሱ ጦር የሽግግር መንግሥት ተብዬው ጦር መሆኑን እንዲቀበሉ አድርጎ፤ የኤርትራን ግንጠላ አረጋግጦ፤ በርከት ያሉትን አደናግሮና ልጆቼ እስኪሉት አሞኝቶ አምባገነን አገዛዙን አጠናከረ። በተለይም ተቀናቃኙን ግን በጥላቻ የታወረውን አነግን ምንኛ እንዳሞኘውና አደናግሮም እንዳጠቃው የምናውቀው ነው። ወያኔ ቁጥሩና ድጋፉ ከኢትዮጵያ አንጻር ደቃቅ መሆኑን ያውቃልና ሰፊው ህዝብ ይወደኛል በሚል ራሱን አያደናግርምና ሕዝብን መከፋፈልና አቅጣጫ ማሳት ተልዕኮውና የሚተማመንበት ነው። ሰርቶለታልም።

አቅጣጫ ማሳት ምን ማለት ነው? ትኩረትን በሣሩ ላይ አድርጎ ገደሉን ከበሬው መደበቅና ማሞኘት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይካሄዳል? ለወያኔ የሞት ሽረት ጉዳይ ነውናም በዚህ ስምሪት ተክኗል፤ መጽሓፍትም ከትቧል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ የማደናገርና ትኩረት የማስቀየር ስልቱና እንቅስቃሴውም የንቃተ ህሊናቸው ደካማ የሆነውን ብቻ ሳይሆን ነቃን አውቅን፤ ምሁር ልሂቅ፤ ተቃዋሚ የሕዝብ መሪ በሉን የሚሉትንም ሰለባ አድርጎ ለስላቅ ዳርጓቸዋል። በ1997-ኡ ምርጫ ጊዜ የሙት ከተማ አድማን አክሽፈው ከወያኔ ሟቹ ቀጣፊ ጋር የረባ ድርድር ይካሄዳል ብለው የቋመጡት ወደዱም ጠሉም ወያኔን እንደጠቀሙና የሕዝብን ወሳኝ ትግል ግን መቀመቅ እንደከተቱ በምጸት የምናስታውሰው ነው። በዜጎች ሬሳ ላይ ተረማምዶና ማወቅ የሚገባቸውን አደናግሮ፤ ጥቂቶችንም በሆዳቸውና በፓርላማ ወንበር ገዝቶ ባለጌ አገዛዙን በራሳችን ላይ በቀጣይነት ሊጭን ችሏል። የማቹ ዘረኛ የወያኔ ቁንጮ ባለቤት "የባሌ የወር ደሞዝ 4ሺ ብር ነው" ልጆቼን ማስተማሪያ ገንዘብ አጠረኝ ስትል የዋሾ ዋሾ መሆኗን ለማረጋገጥ ፈልጋ ሳይሆን ሕዝብን ሞኝ አድርጋ ወስዳ የወያኔ ማደናገር ሁሌም ይሠራል በሚል እምነት ነው። ወያኔ ሕዝብን መናቁ ደግሞ የአደባባይ ምስጢር መሆኑ አይካድም። የተነሳውን ተቃውሞ ሁሉ ደም አፍሶ ስለሚያፍን ፤ አርድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመጽ ገና ስላልተከሰተ፤ ቢያፍስ ቢረሽን የሚደርስበት አጸፋ ባለመኖሩ፤ ተለጣፊና አደግዳጊ ማፍራት በመቻሉ፤

በሰርጎ ገቦችና በታኝ- አንጃዎች ድርጅቶችን ማዳከም ስለቻለ፤ የሀገርን መሬት ለሱዳን ሲሸጥ፤ ለቻይና፣ ለህንድና አረቦች ሲቸረችርና ሕዝብን ሲያፈናቅል፤ የሃይማኖት ተቋሞችንና አማኞችን ሲደፍር ሲረግጥ፣ ሲያስር ሲበድል፣ ስነ ምግባር ለጎደለው አረብ ቱጃር ሕዝብን አዋርድ ብሎ ሲፈቅድ፤ ህጻናትንና ወጣት ሴቶችን ሲሸጥ፤ የሀገራችንን መሬት የባዕድ ጦር መስፈሪያ ሲያደርግ አሁንስ በዛ ብሎ የሚያምጽ በማነሱና ይባስ ብለውም ሰላም ሰላም እያሉ የሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሀ የሚቸልሱ በመብዛታቸው የወያኔ ንቀትና እብሪት ከዳሸን ተራራ ተልቋል። ወያኔ ነጋ ጠባ ወይም አስፈላጊ በሆነበት ማደናገሪያውን ይፈለፍላል። ይህን ባደረገም ቁጥር ኢሕአፓ ተንኮሉን አጋልጦ አንሞኝለት ሲል አስጠንቅቆ ነበርም--አሁንም እያደረገ ነው።

በቅርቡ ይዞ የተነሳውን የአባይ ግድብና የሙስና አፈሳ ማደናገሪያዎችም መጥቀስ የሚገባን ነው። የፈረደበትን አማራ በጥላቻ ካፈናቀለ በኋላ ተቃውሞ ሲፋፋም በሙስና እነ እገሌን አፍሰናል ብሎ በመንጫጫት የብዙዎቹን ትኩረት አቅጣጫ ቀየረ። የታገቱት የወያኔ የውስጣዊ ችግርና ቀውስ ሰለባዎች እንዳሉ ሆኖማደናገሪያ/መጠፊያ መሆናቸው ደግሞ ለማንም ግልጽ ነው። ዋናዋ የሙስና እቴጌ እያለች፤ ሀፍረተ ቢስና ይሉኝታ ያጡ በሙስና የተጨማለቁ ዋና ዋና ወያኔዎች እያሉ ድምቢጦችን አፍሶ ጨኸት ማፋፋሙ ግቡ የሕዝብንና የዓለምንም ትኩረት ከአማራው ጥቃት ለማንሳትና ለመቀየር መሆኑ ግልጽ ነበር--በከፊልም ሰርቷል ብንል ስህተት አይሆንም።

የሕዝብ ትኩረት የወያኔን አገዛዝ በማስወገድ ላይ መሆን ያለበት ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶችም ዋና ትኩረታቸው ከፋፋዮችንና የወያኔ ሰርጎ ገቦችን አስወግደውና ድክመታቸውን አቸንፈው በጋራ ትግል ላይ መሰማራት ነው። ከዚህ አስፈላጊና ሀገር አድን ትኩረት የሚያግድ ማንኛውም የወያኔ ሴራና እንቅስቃሴ ለወያኔ ወርቅ ነው። በአረብ ሀገሮች/ሰሜን አፍሪካ ዛሬ ቢደናቀፍም የሕዝብ አመጽ ተፋፍሞ እየተስፋፋ ስለነበር ይህም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይዘልቅ የፈሩት ወያኔዎች የአባይ ግድብ የሚል ማደናገሪያን ይዘው በመነሳት፤ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም እቅድ የሚይዙ አስመስለው በመመጻደቅ ለማደናገር ችለዋል። በግብጽና ሱዳን ሙሉ ድጋፍ ለሥልጣን የበውቃው ወያኔ፤ ሥልጣን እንደያዘም አባይን በተመለከተ ከሙባረክ/ግብጽ ጋር ገጥሞ የነበረው፤ የሀገራችንን መሬት ለሱዳን የሸጠው፤ ለህንድና ቻይና፣ ...ወዘተን መረን ለቆ ስንት ሺውን ያፈናቀለው ወያኔ፣ ከመቅጽበት ለሚጠላት ኢትዮጵያ አሳቢ ይሆናል/ሆነ ብሎ መገመት ራሱ ከስህተት በላይ ቅዠት ሆኖ ሳለ አባይም ይገደባል፤ ከወያኔ ጎን ቆመን ደማችን ግብጽን ለመከላከል ይፈሳል የሚሉ ተቃዋሚዎች ወይም ነቃን ባይ ምሁር በሉን ባዮች ብቅ ብቅ ብለዋል። ወያኔ እውን ግድቡን ሊሰራ ካሰበ 4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ድሀ ሕዝባችን ላይ ጭኖ መከራን ከማባባስ ለምንስ ከዘረፈው ገንዘብ ወጪውን አይሸፍንም? ለምንስ ሱዳን ድንበር አጠገብ ሄዶ ግድብ ልስራ ይላል ? ኢትዮጵያ የጥቁር አባይ ምንጭ ብትሆንም ብቸኛ የአባይ ባለቤት አይደለችም-- ውሀ አጠቃቀምን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ህጎች ኣሉ--ግብጽም ብትሆን ይህን መካድና መሻር አትችልም። አባይ ከመገደቡ በፊት የወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ይውደቅ ማለቱ ሲገባ በሌለ አቅምና አላስፈላጊና ጎጂ በሆነ ጎዳና ወደ ግጭት መንጎድ ስህተት ነው፤ ዳግም በወያኔ መደናገር ነው ሲል ኢሕአፓ አሁንም እያሳሰበ ነው።

ወያኔ ለሥልጣን ከበቃ በኋላ የኢትዮጵያ መከራና ስቃይ መረን ለቆ መባዛቱ፣ መብዛቱ የሚካድ አይደለም። የሕዝብና የሀገር ጠላት የወያኔ አገዛዝ ነው ። ግብጽ ሆነ ሌላ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመደቡ አይደሉም። ዝንጅሮ በቅድሚያ የመቀመጫዬን እንዳለችው የሕዝብ ዋና ትኩረትና ግዳጅ መሆን ያለበት ወያኔ ጠላት መሆኑን አውቆ አምርሮ--ሳይደናገሩ-በመታገል ማሸነፍና መጣል ነው። ይህ ንቃትን፤ ለወያኔ ተንኮል ሰለባ አለመሆንን ይጠይቃል። በተያያዘም ደግሞ የሀገራችን ሕዝብ የቆየ አንድነት ታድሶ መቀጠል እንዳለበትም ጫና ሰጥቶ መገንዘብ ያስፈልጋል። ኢሕአፓ ትብብርና አንድነትን በተመለከተ ከአፄው ጊዜ ጀምሮ ያደረገው ጥረትና አስተዋጾ፤ የተገኘውም ውጤት የሚካድ አይደለም። ድርጅቱ በፖለቲካ

መደራጀትን በተመለከተ፤ የሴቶችን ተሳትፎ በማጠናከር፤ ፖለቲካዊ ንቃትን በማስፋፋት፤ ጽናትና ወኔን፣ ኣይፈሬ ሞት መሆንን በማስፈን በተጨባጭና መራራ ትግል መስዋዕትነት የትግልን ይዘትና ትርጉምም አድሶ አስተምሯል። የነ ተስፋዬ ታደስ፣ አሰፋ ማሩም ሆነ የነጋይም መስዋዕት መሆን የሚያስተምረውም ይህንኑ ነው። ዛሬም ያ ጽናት፤ ያ ወኔ፤ ያ የማያወላውል የሕዝብና የሀገር ፍቅር እውን እንዲሆን እየታገለ አለ ። በተጨባጭ ፀረ ወያኔ ኅብረት እውን ሆኖ አገዛዙን እንዲገረስስ በተደረገው ጥረት ውስጥ ኢሕአፓ የተጫወተው አቢይ ሚና አልነበረም ተብሎ የሚሰረዝ አይደለም - ምን ያህል ቢዋሽና የክስ ጣት ቢቀሰር። ኢሕአፓ በበርካታ የኅብረት ጥረቶች ውስጥ ግምባር ቀደም ሚና ተጫውቷል። ኢሕአፓ ግን መቼም ቢሆን መቼ ከሕዝብ ጠላቶች ጋር አላበረም--ከደርግም ሆነ ከወያኔ ጎን አልተለጠፈም። ስንቶቹ ሌሎቹ ዛሬ ተቃዋሚ ነን የሚሉት ይህን ማለት ይችላሉ?

ሲጠቃለል ኢሕአፓ ራሱን ለማሞገስና ማንም አይደርስብኝም ብሎ ለመታበይ ሳይሆን ለ40 ዓመታት ያካሄደው መራራና መስዋዕትነትን ያስከፈለ ትግል የለገሰው ሰፊ ተመክሮ መደረግ ላለበት ትግል ቅርስና ትጥቅ ነው የሚለውን ጫና ሰጥቶ ለማቅረብ ነው። እግረመንገድም አይታከቴ ዋሾዎችንም ሐቁን ነግሮ --የዋሾ የለመደ ምላስ አይታከምም ቢባልም--የሰማዕትን ታሪክ ለማስከበር ነው።

ከመጠምጠምና ከመለፍለፍ
መማር ማወቅ ይቅደም ለማለት።

ትግላችን ይቀጥላል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን ያቸንፋል !!__